<u>ቪቫ አያልነሽ !</u>
<u>ወደ ተግባር እንሸጋገር !!</u>

*ከአስተዋይ በቀለ*

በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓላማ ክፉና ፈታኝ ወቅት ሴቶች ብቅ እያሉ አገርን በማዳኑ ብሔራዊ ተግባር ባልተቆጠበ ቆራጥነትና ጀግንነት እየተሳተፉ ሕያው የሆነ አብይ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ታላቁ አኩሪው ታሪካችንና የዘመናት የፖለቲካ ሕልውናችን ያስረዳል።

ዛሬም እንደትናንቱ እናት ኢትዮጵያን ከአጥፊዎቿ ለማዳን በመራራ የሜዳ ትግል የተቀረጹና እስከ የሕይወት መስዋዕትነት መክፈል ድረስ ተዘጋጅተው በተጠንቀቅ ላይ የሚገኙ ብዙ ሲሆኑ፤ ከመካከላቸው አንዷ፣ እውቋና ዝነኛዋ አያልነሽ ናት።

ኢትዮጵያ የሞተልሽ ቀርቶ ሆኖ ነው እንጂ ሁኔታው፤ አያልነሽ ከትግል ፈታኝ ሜዳ የወጣች፣ ዝነኛ፣ የዘመናችን ብሔራዊ ሕዝባዊ ጀግና ናት። አገር ስትድን ገድሏ ፈክቶ ይወጣና ትክክለኛውን እውቅናና ታሪካዊ ቦታ በመያዝ የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ኩራትና አርአያ ሆኖ ይወደሳል።

አያልነሽ ጀግና ብቻ ሳትሆን ከበረሃ እስከ ስደት በተካበተ የትግል ልምድና ማስተዋል የተካነች፣ ገንቢ ትችት አፍቃሪ፣ በሕዝብ ላይ ከፍተኛ እምነት ያላትና ከጎኑ አብራ የቆመች፣ አገር የማዳን ግዴታዋን፣ ኃላፊነቷን፣ የፖለቲካ መስመሯንና ጉዞዋን የተረዳች፣ ትግሉን ዳር ለማድረስ በጽኑ የቆመችና አርቆ አስተዋይ ናት።

“ቸገረን እኮ !..... ” በተሰኘው ጽሑፏ ውስጥ ያስመረችባቸው ጉዳዮችና አርቀው ያዩ ሀሳቦች ሁሉ ሊተኰርባቸው የሚገቡ ማሳሰቢያዎች ናቸው።

ኢትዮጵያ፣ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅዓላማን እናድን ካልን አያልነሽ እንዳሳሰበችው “...ተሞክሮ ተሞክሮ አልሰራ ያለ...” እና “... እየፈጩ ጥሬ ጉዞአችንን...” ትተን ወደ ወሳኝ ብሔራዊ፣ ሕዝባዊ አገር የማዳን ተግባር በአጣዳፊ መሸጋገር፣ መደራጀት፣ መዘጋጀት፣ በግልጽና በስውር በስፋት መንቀሳቀስ እጅግ አስፈላጊና ከአሁኑ ጀምሮ ነው።

ጠላትን መፈንቀል፣ ስልጣን ማሸጋገር፣ ማረጋጋት፣ የገንዘብ-የንብረት-የባለስልጣንና- የወንጀለኞች ሽሽትን መግታት፣ ሌባ ቦዘኔን ማሳረፍ፣ አሮጌውን ማፍረስ፣ መስተዳድር መዘርጋት፣ ቁልፍ የመገናኛ-የመከላከያ-የደህንነት ወዘተ... ተቋሞችን መቆጣጠርና ስትራቴጂክ ቦታዎችን መሸፈን፣ ተቃውሞንና ያልተጠበቁ አፍራሽ

ሁኔታዎችን ማምከን፣ የሰው ኃይል መመደብ፣ ለአስከፊ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች አጣዳፊ መፍትሔ መስጠት፣ አገርን መጠበቅ፣ በክፍለ ሀገር- በአውራጃ- በወረዳ በምክትል ወረዳ- በቀበሌ- በጠረፍ ነጥብ ጣቢያዎች ሌጂትሜሲን ማረጋገጥና ሕጋዊ እውቅናን ከመንግሥታት ማግኘት ወዘተ… የመሳሰሉ ብሔራዊ፣ አገራዊ ጉዳዮች ሁሉ ከአሁኑ አበክሮ መደራጀትን፣ መዘጋጀትንና እያንዳንዱ ኃላፊነቱንና ግዴታውን አውቆ በዚያች ቀውጢ ሰዓት ቦታውን ለመሸፈንና ኃላፊነቱን ለመወጣት በተጠንቀቅ ላይ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል።

አገርን የሚያድን አይነተኛ ዋስትና ይህን የመሰለ ተግባራዊ እርምጃ ሲሆን፤ አፈጻጸሙ ጥንቃቄ ይጠይቃል። በተለይ የራስ ወገንና የትግል አጋር ሆነው ወይንም መስለው አገር በማዳኑ ጉያ ውስጥ እሳት እያነደዱ አላሰራ በሚሉት ላይ የማያዳግም ቀዳሚ ጥንቃቄ ካልተወሰደ ውሎ አድሮ የእርድ ሰንጋ የፍሪዳ በሬ መሆንን ያስከትላል። ስለዚህ አያልነሽ እንዳለችው ጉዞአችን እየፈጩ ጥሬ እንዳይሆንና ትግሉም ዳር ሳይደርስ እንዳይሰናከል ብዙ ነገሮችን በጥሞና ልብ ማለትና አተኩሮ ማስተዋል ያስፈልጋል።

*ቪቫ አያልነሽ!*

*ቪቫ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና*

*ሰንደቅ ዓላማ!!!*